# አልቅሱ?

አልቅሱ ይለናል መልካም እነደሠራ፤

የብዙ ንጹህ ደም በከንቱ እንዳልዘራ፤

አልቅሱ፤ አልቅሱ፤ አልቅሱ ይለናል፤

ተግባርና ታሪክ ባልዋለበት ውሏል፤

አንተው አልቅስ እንጂ እንደፈረደብህ፤

ነገ በጥዋቱ መድረረሻ ሊጠፋህ፤

ህዝብን እንደዋዛ ደግሞ መጎተትህ።

የቱልቱላ መንጋ የወሬ መሰንቆ፤

ሀሰትን ሰንቆ ውሸትን ሸምቆ፤

የሆነ ያልሆነ ለኛ ቢያወራልን፤

እውንት ፈሯን አትስት ከቶ ምን አለፋን!

አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፤

የሞተልስ ቀርቶ የገደለሽ በላ፤

እንደተባለውም ጥንት ካባቶች፤

አልቅሱ ይለናል የመከራው አዝማች።

ድሀ ፈረደበት እንባውን ያምጣል፤

ረሀብ ጠኔ ግቶት አልቅስም ይባላል፤

በቁሙ ዘልዝሎ መከራ እንዳልጋተው፤

አልቅስ በሚለው ፌዝ ዳግመኛ ሞገተው።

እርሱማ ያለቅሳል ለርሱ መስሎት እንዴ፤

ለሞቱት እኮ ነው ይረዳህ ወልጋዴ፤

ለጨፈጨፉቸው ለመካራ ገልጦ፤

ለተጎዳች አገር ጥሪቷን አሟጦ፤

አንክቶ ለበናት ውስጧን ሳነቀዛት፤

ለትውልድ ለዘመን ለሚዘልቀው ጥፋት።

አልቅሱ ይለዋል በድንኳን ከትሞ፤

ተረስቶ ተቀብሮ የግፍ ስራው ከርሞ፤

አይነጋ መስሎታል ይነጋል ይነጋል፤

የሚስጥር ግድያው አፈናው ይወጣል፤

ነጣነት ሲመጣ ሁሉም ይነገራል።

አልቅሱ አልቁሱ አልቅሱ ይለዋል፤

አረ ለነገሩ እንባ እንዴት ይማጣል፤

ያውም ለገደለን አገርን ሳጠፋ፤

ባደባባይ ሁሉ ልፈፋ በይፋ፤

አልቅሱ ይባላል በግድ በደረቁ፤

ስንት ግፍ ተረስቶ መቸም አላወቁ፤

አይባልም እኮ ያውቃሉ በቅጡ፤

ምን ለማለባበስ ቢወርዱ ቢወጡ፤

ይነጋል ይበራል አይቀርም በላቸው፤

የት እንደሚገቡ ሲወጣ ጉዳቸው።

አልቅሱ፤ አልቅሱ አልቅሱ ይበለን?

የዘመናቱ ግፍ እንደምን ይረሳን፤

አንደምን ተደርጎ አልቅሱ ይባላል፤

ባዋጅ ይለፍፋል፤ ሰው እዴት ይረሳል፤

የደረሰበትን የዋለውን ሁሉ፤

የኛ ህዝብ አይረሳም ታዘቡ ጉድ በሉ።

ተቀለደ እንጂ ተፌዘ ተሳቀ፤

የውሸት አታሞ እየተደለቀ፤

የገደለን ጨካኝ እንዳዳነ ሁሉ፤

አልቅሱ የሚል ፌዝ በቅዠት ከዋሉ።

ሕዝብን ጨፍጭፈሀል አገር ገንጥለሀል፤

ድንበርስ ሸጠሀል ታሪክን ሽረሀል፤

ንጹሀን በጅምላ በግፍ አግዘሀል፤

በጥይት በረሀም ድሀን አምሰሃል፤

የትውልድን ተስፋ ጭለማ አልብሰሀል፤

የጊዜ ፈንጅውን ባለበት ቀብረሃል፤

ከብዙ በጥቂት ይኸ ይበቃሃል፤

ዳግም ጨርቅ ባልከው ተጠቅልለኸዋል፤

ህዝብ ቢያለቅስ ቢቆዝም እውነት ይመስልሀል?

ማዘን መራራት ነው፤

ሰብእና ምግባር ነው፤

እንባም ካንጀት ሲሆን፤

ነበር መተዛዘን፤

በግድ እየገፉ ባደባባይ ሁሉ፤

አልቅሱ ምንድን ነው አገር አንድ በሉ!

ሥጋውም ይበላ ጠጁም ይጠጣና፤

ትዝብቱ ይቀራል አይኑን ያፈጥና።

አገርን ለመምራት ማንም ይመራታል፤

ውጤቱ ነው እንጂ ወሬማ ተወርቷል፤

ውሸትም ተዘርቷል እንደምን ይበቅላል፤

ማእበል ሲመጣ ነውጥም ይናወጣል፤

ብትንትኑ ወጥቶ ይፈርሳል ይናዳል፤

ጠመንጃማ ቢያድን ዘላለም ይኖራል፤

ብልን ነበር ትላንት ሰሚ ከተከኘ፤

ሰውኮ አይደለም አባት ከላይ ዳኘ።

ዳኛው አባታችን ብዙ ጉድ ያሳያል፤

በሙቱ አይደለም በቁም ይቀብራዋል፤

አይኖሩ ይኖራል አይሞቱ ይሞታል፤

ህዝብን ያስለቀሰ መውደቁ ይከፋል።

የጭቆናን ቀንበር ያፈርሳል ይሰብራል፤

ሕዝቡን ለነጻነት አርነት ያወጣል፤

ጠመንጃና ጥይት ከቶ ሰው ያተርፋል?

ያስመካል ያድናል?

ወይስ ይሸሽጋል?

ቢሆንማ ኑሮ እንዳለ ሊቀጥል፤

ነበረ መቃዠት ባልሆነበት ሊዋል፤

**ቢወጣና ቢወርድ የማይሆን አይሆንም፤**

**ምንጊዜም የእውነት ዘንግ ወድቃ አትሰበርም።**

ለመልካም በመልካም እንባ መች ይገዳል፤

**ዘጠና ዘጠኙ ሳቅም አልቅስ ሲባል፤**

**አይተናል ሰምተናል ሁሉን ታዝበናል፤**

ዘሬም ታልፋታለች ነገም ብቅ ስትል፤

ምን ሊወራ ይሆን ከቶ ምንስ ሊባል።

በበኩል በበኩል ለሕዝብ የታዘናል፤

በጎራ በጎራ ላገር ይተመማል፤

ለድሀ ለሚኞችታስቦ ይነባል፤

ለትውልድ ለታሪክ አዲስ ይቀመራል፤

ሌላውን አናውቅም ከቶ ምኑን ገዶህ፤

ለገደለህ ማልቀስ ክፉ ለዋለብህ።

የቱልቱላ ብዛት የወሬ መሰንቆ፤

ውሸትና ከንቱ ሸምቆ ሰናንቆ፤

**ቢከፍት በህዝባችን የወሬ ዘመቻ፤**

**እውነት አትቀየር በዛቻ ባሳቻ!!**

ፍ.አ

08 27 2012